Minnesota Department of Health • የባዮቴሮሪዝም መረጃ 10/8/2005

# ፈንጣጣ

## ፈንጣጣ ምን ያክል አስጊ ነው?

የፈንጣጣ መለያ ትኩሳትና የተለየ ዓይነት ሽፍታ ሲሆን በአንድ ወቅት የሰውን ልጅ ከሚያሰጉት በሽታዎች ዋናው ነበር። ፈንጣጣ በቫይረስ የሚከሰት በሽታ ሲሆን፣ በሽታው የያዛቸው ሰዎች እስከ አንድ ሶስተኛው ይሞቱ ነበር።



*የፈንጣጣ ክትባት*

ሆኖም የወርልድ ሄልዝ ኦርጋናይዜሽን ባደረገው ታላቅ ዘመቻ አማካኝነት ከ1980 ዓ.ም. በፊት ፈንጣጣ ለሕዝብ አስጊ እንዳይሆን ተወግዷል። በዓለም ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ሰዉ ላይ የተገኘው በ1970ዓ.ም. ማለቂያ ላይ ነው። ከሰዎች በስተቀር እንስሶች ላይ ፈንጣጣ ስለማይገኝና በእንስሶች ስለማይተላለፍ በሽታውን የመያዙ አስጊነት ወደ ዜሮ ተቀንሷል።

ይህም ሆኖ ፈንጣጣን ሙሉ በሙሉ አልፈነዋል ለማለት ያዳግታል። በሽታው ከጠፋ በኋላ ለናሙና ያክል የፈንጣጣ ቫይረስ ቤተ ሙከራ ውስጥ ተቀምጦ ስለነበር አሁን ቫይረሱ ለጦር መሣሪያነት እንዲውል ተደርጎ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ቫይረሱን አውቆ በመልቀቅ የፈንጣጣ በሽታን ማራባት እውነት ሊከሰት የሚችል ነገር ነው ተብሎ ይገመታል። ዐመጸኞች ፈንጣጣን ተጠቅመው ሽብር የፈጥራሉ ተብሎ የሚታሰበው በጣም በትንሹ ነው። ሆኖም ይህ ዓይነት ጥቃት ቢፈጠር በጣም አሳሳቢ ሁኔታ ሊያስከትል ይችላል።

## የፈንጣጣ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

ፈንጣጣ ሲጀምር የሚታዩት ምልክቶች ኃይለኛ ትኩሳት፣ የጭንቅላትና የሰውነት ሕመምና አልፎ አልፎም ማስታወክ ናቸው። ከሁለት እስከ አራት ቀናት በኋላ ሽፍታ መታየት ይጀምራል። ሽፍታው ይባዛና ጉብ ጉብ ብለው ደርቀው ወደሚቀረፉ እብጠቶች ይቀየራል። ከሶስት ሳምንት በኋላ ቅርፊቶቹ ይወድቁና ጎድጓዳ ጠባሳዎች የተዋሉ።

## ለበሽታው ከተጋለጡ በኋላ ፈንጣጣ እስከሚይዝ ድረስ ስንት ጊዜ ይፈጃል?

## ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚቻለውስ መቼ ነው?

አንድ ሰው ለበሽታው ከተጋለጠ በኋላ የፈንጣጣ ምልክቶች እስከሚታዩ ድረስ ከ12 እስክ 14 ቀኖች ይፈጃል። አንዳንድ ጊዜ ግን በሰባት ቀን ጊዜ ውስጥ ወይም ከ17 ቀን በኋላ ሊታይ የችላል። አንዴ ምልክቶቹ ከታዩ በኋላ በሽታኛው በጣም ስለሚታመም መንገድ ለመሄድ ወይም እለታዊ እንቅስቃሴዎቹን ለማድረግ ይሳነዋል። ሽፍታው እስከሚታይ ድረስ ግን በሽተኛው ለሌች ሰዎች በሽታውን አያጋባም።

## ፈንጣጣ ምን ያህል ተላላፊ ነው?

ፈንጣጣ ተላላፊ ቢሆንም የጉንፋንን ወይም የኩፍኝን ያህል ተላላፊ አይደለም። በአጠቃላይ በሽታውን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ ለረጅም ጊዜ ፊት ለፊት መገናኘት አለበት - ለምሳሌ በቤት ውስጥ ሊፈጠር ይችላል። ከሰውነት የሚወጡ ፈሳሾችን በመንካት ወይም በአንሶላና በልብስ በመሳሰሉ እቃዎች ሊተላለፍ ይችላል። የተለመደ ባይሆንም ሕንጻዎች ውስጥ ወይም ሌላ ተመሳሳይ የተከለለ ቦታ ውስጥ በሚገኝ አየር ሊተላለፍ ይችላል።

## ፈንጣጣ ሕክምና አለው?

በአሁኑ ጊዜ ለፈንጣጣ የተረጋገጠ ሕክምና የለም። ሆኖም በሽታውን በክትባት መከላከል ይቻላል።

ክትባቱ ለፈንጣጣ ቫይረስ ከተጋለጡም በኋላ ከበሽታው ሊከላከል ይችላል። ፍጹም መከላከያ የሚሰጥ ምንም ዓይነት ክትባት ባይኖርም፣ ለፈንጣጣ ከተጋለጡ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ክትባት መውሰድ ለበሽታው ከመጋልጥዎ በፊት ክትባቱን እንደወሰዱት ያህል ይካላከላል። እስከ ሰባት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ክትባቱን መውሰድ ለፈንጣጣ ከመጋለጥ ከሚመጣው የሕመም ጉዳት ይቀንሳል። .

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

ሆኖም ክትባቱ በአንዳንድ ሰው ላይ መጥፎ ዓይነት አንዳንዴም እስከ ሞት የሚያደርስ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል ጥቅሙና ጉዳቱ እየታየ መደረግ ይኖርበታል። እስከዛሬ እንደተገመተው ክትባቱን ከሚወስዱ ከ15 ሚሊዮን ሰዎች ቢያንስ አንድ ሰው ይሞታል፣ 15 ደግሞ በጠና ይታመማሉ። አንድ ሰዉ በሽታውን እንደ ጦር መሣሪያ ካልተጠቀመው በስተቀር ፈንጣጣ ጭራሽ ሊይዝ አይችልም።